# “ገሃነም ውስጥ እንደመኖር’’

## ፖሊሶች በካሌይ የሚገኙ ህጻናት እና አዋቂ ስደተኞች ላይ ሰበአዊ ጥቃት ይፈጽማሉ።

# ማጠቃለያ

> የካሌይ ካምፕን ባለፈው አመት ካፈረሱት በኋላ የምንበላበትም ሆነ የምንተኛበት ቦታ የለም። ኑሯችን ልክ ገሃነም ዉስጥ የመኖር ያህል ከባድ ነው።
>
> –ያዕቆብ ሰ፣ የ29 ዓመቱ ኢትዮጵያዊ፣ ሰኔ 30,2017

> በቅድሚያ እዚህ የመጡት ወንዶች እና ሴቶች ከሶሪያ የፈለሱ ስድተኞች ናቸው፤ አሁን ደግሞ ከኤርትራ እና ሌሎች በርካታ ሀገራት ለነጻነታቸው ሲታገሉ የነበሩ ሰዎች እየመጡ ይገኛሉ ስለሆነም በአውሮፓ እና በተለይም በፈረንሳይ ተቀባይነት ሊያገኙ ይገባል።
>
> –ፕሬዝዳንት ኢማኑኤል ማክሮን፣ትሬስቴ ጣልያን፣ ሓምሌ 13, 2017

የፈረንሳይ ባለስልጣናት በካሌይ ጫፍ የሚገኘውን እና ''ጫካው'' በመባል የሚታወቀዉን ትልቁን የስደተኞች ካምፕ ከዘጉ ከዘጠኝ ወር በኋላ ከ400 እስከ 500 የሚሆኑ ስደተኞች እና ከለላ ፈላጊዎች በሰሜናዊ የፈረንሳይ ከተማ ጎዳናዎች እና ጫካዎች ዉስጥ እየኖሩ ይገኛሉ።

ይሄ ዘገባ በካሌይ እና ዳንኬርክ አከባቢ የሚኖሩ ከ60 በላይ ከለላ ፈላጊዎች እና ስደተኞች እንዲሁም ሁለት ደርዘን የዕርዳታ ሰራተኞች ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ ላይ በመመስረት የፈረንሳይ ፖሊሶች ከለላ ፈላጊዎች እና ስደተኞች ላይ የሚፈጽሙትን ሰብአዊ ጥቃት፣ በአካባቢው የሚከናወን የሰብአዊ ተራዳኦ ድጋፍን የማሰናከል ተግባር እና የዕርዳታ ሰራተኞች ላይ የፈጸሙትን ትንኮሳ ያትታል። ባመዛኙ እነዚህን የመሳሰሉ ተግባራት የሚከናወኑት በአካባቢው የስደተኞችን ቁጥር ለመቀነስ ባለቻው ፍላጎት ምክንያት ነው።

ሂዩማን ራይትስ ወች ያደረገው ጥናት ዉጤት እንደሚያሳየው በካሌይ ያሉ ፖሊሶች በተለይም የፈረንሳይ አድማ በታኝ ፖሊሶች ህጻናት እና አዋቂ ስደተኞች ተኝተው በሚግኙበት እና  እና ምንም አይነት አደጋ ሊፈጥሩ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ እያሉ አቃጣይ ፔፐር ስፕሬይ ይረጩባቸዋል፣ ብርድልብሳቸውን፣ የመኝታ ከረጢታቸውን እና ልብሶቻቸውን ይወስዱባቸዋል። አንዳንዴ ደግሞ የስደተኞቹ ምግብ እና ውሃ ላይም አቃጣይ ፔፐር ስፕሬይ ይረጫሉ። የሰብአዊ ተራዳኦ ለስደተኞች አንዳይደርስ ፖሊሶች እንቅፋት እየፈጠሩ ነው። ይህ የፖሊስ ሰብአዊ ጥቃት  የህፃናት ጥበቃ አገልግሎት ማግኘት እና የስደተኞች ከለላ የመጠየቅ ፍላጎት እና አቅም ላይ አሉታዊ ተፅኖ ያሳድራል።

በካሌይ እና አከባቢዋ እየተፈጸመ የሚገኘው እንዲህ አይነት የፖሊስ ጥቃት ሃይልን አላግባብ በመጠቀም ነው፤ከለላ የተደረገለትን ኢ-ሰብአዊ እና አዋራጅ ሰብአዊ አያያዝ ወይንም የቅጣት ሁኔታንም የሚጥስ ነው፤ እንዲሁምየስደተኞች ምግብ እና ዉሃ የማግኘት ሙብትን መከልከል መሰረት የሌለው እና ምንም ዓይነት ምክንያት የማይኖረው የሙብት ጥሰት ነው። የአለማቀፍ መመዘኛ  እንደሚጠይቀው ፖሊሶች ሀይል መጠቀም የሚችሉት በፍጹም የሀይል እርምጃን ማስቀረት የማይቻል ሁኔታ ሲያጋጥም መሆኑን እና ይሄም ቢሆን በመቆጠብ እና ከሁኔታው ጋር ተመጣጠኝ በሆነ መልክ ህግን ለማስፈፀም ሲሆን ብቻ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል።

ባለስልጣን አካላት በስፋት የተዘገበውን እና ፖሊሶች ከለላ ፈላጊዎች እና ስደተኞች ላይ ያደረሱትን ጥቃት በተመለከተ የሰጡት ትኩረት የለም። የካሌይ ምክትል አስተዳዳሪ ቫንሳን ቤርቶን ፖሊሶች ፈጸሙት የተባለዉን አቃጣይ ፔፐር ስፕሬ እና ሌሎች ያልተመጣጠነ የዘፈቀዳዊ የሀይል እርምጃዎች እዉነትነት የሌላቸው የግለሰቦች የፈጠራ ክስ ነው ብለዋል ለሂዩማን ራይትስ ወች በሰጡት ቃል።

በመጋቢት ወር 2017፣ የአከባቢው ባለስልጣናት የሰብአዊ ተራደኦ ቡድኖች ምግብ፣ ዉሃ፣ ብርድ-ልብስ እና አልባሳትን እንዳያከፋፍሉ አግደው ነበር። ይሄ ድርጊት ከኢሰብአዊ እና አዋራጅ አያየዝ ጋር ይስተካከላል በማለት መጋቢት 22 ፍርድ ቤት ዉሳኔው እንዲቀለበስ አድርጓል። የፈረንሳይ እምባ ጠባቂ ተቋምም ይሄን እና ሌሎች የካሌይ አስተዳዳሪዎች የተወሰዱትን እርምጃዎች በመተቸት በካሌይ የሚገኙ ስደተኞች እና ከለላ ፈላጊዎች ኢሰብአዊ ኑሮ እንዲኖሩ አስተወጽዖ ያደርጋል በሚልኮንኗል።

ከሰኔ ወር መጨረሻ ጀምሮ ባለስልጣናቱ የድሮ ስደተኞች ካምፕ አቅራቢያ ባለው የኢንዱስትሪ አከባቢ ዉስጥ በቀን አንዴ ለሁለት ሰዓት ብቻ የሰብአዊ ተራዳኦ ድጋፍ ለስደተኞቹ እንዲደርስ ፈቅደዋል። ከዚህ በተጨማሪ አንድ የአከባቢው ቄስ ቤተስክያን ዉስጥ በምሳ ሰዓት የተራዳኦ ቁሶችን እንድያከፋፊሉ ፈቅደዋል። ከዚህ ዉጭ ያለዉ የሰብአዊ ተራድኦ ድጋፎች ስደተኞች ጋር እንዳይደርስ ፖሊሶች በተደጋጋሚ እቀባ ያደረጋሉ። የዕርዳታ ሰራተኞች አንድ ቀን ከባድ መሳሪያ በታጠቁ የጸጥታ ሀይሎች መከበባቸውን እና ስደተኞች የዕርዳታ ሰራተኞችን እንዳያገኙ በተደጋጋሚ መከልከላቸዉን እና ለስደተኞች ምግብ ለማቀበል ሲሞክሩ ከእጃቸው ምግቡን ነጥቀው መወርወራቸውን ይናገራሉ።

የፈረንሳይ ህግ በሚፈቅዳላቸው መሰረት የዕርዳታ ሰራተኞች አንደዚህ አይነት የፖሊስ ድርጊቶችን በፎቶ እና ቪዲዮ ቀርጸው ማስቀመጥ ጀምረዋል። በምላሹም ፖሊሶች ሞባይላቸውን ለተወሰና ግዜ በመንጠቅ ካለ ምንም ፈቃድ ስልኮቹን በመበርበር መረጃዎችን ከስልኩ እያጠፉ መሆኑን የሰብአዊ ተራድኦ ሰራተኞች ተናግረዋል።

የዕርዳታ ሰረተኞች በየግዜው ለመታወቅያ ፍተሻ እንደሚዳረጉ ይናገራሉ። አንዳንድ ጊዜ ፖሊሶች ብዙ ሰዓት የሚፈጅ ሁለት እና ከዚያ በላይ ፍተሻ ያደርጉባቸዋል። የማንነት ምርመራ በፈረንሳይ ህጋዊ ነው ነገር ግን በፖሊሶች ያልአግባብ ለመበደል ተጋላጭ ነው። በካሌይ የሚደረግ የዕርዳታ ሰራተኞች የማንነት ፍተሻ የሰብአዊ ተራድኦ ድጋፍ ስርጭትን ወደ ኃላ ጎትቶታል። ከሰብአዊ ድጋፍ ስርጭት በኃላ ፖሊሶች እንዴት ስደተኞቹን እንደሚበትኑ እንዳየታዝቡ ፖሊሶች እንደሚከለክሏቸው የሰብአዊ ተራድኦ ሰራተኞች ተናግረዋል።

ፕሬዝዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ሰብአዊነት ያለው የስደተኞች እና ከለላ ፈላጊዎች አያየዝን ቃል ገብተዋል። የእርሳቸው አስተዳዳር ለስደተኞች እና አብረዋቸው ለመጡ ህጻናት ጥገኝነት የመጠየቅ ሂደቱ እንዲሻሻል፤ ተጨማሪ የመኖሪያ አቅርቦት እንዲመቻች እና ሌሎች ድጋፎች እንዲጠናከሩ እንደሚሰሩ ቃል ገብቷል። እናኝህ ጥሩ እርምጃዎች በአሁኑ ወቅት በካሌይ የሚገኙት ከለላ ፈላጊዎች እና ሌሎች ስደተኞች እያዩ ካለው መከራ ጋር ይጣራሳሉ።

እነኝህን ቃልኪዳኖች እና አለም አቀፍ የፈረንሳይ ግዴታዎች ለመፈጸም  የአከባቢው እና የሀገሪቱ ባለስልጣናት ፖሊሶች የሀይል እርምጃ አወሳሰድ ላይ የአለም አቀፍ የፖሊስ የሀይል እርምጃ አወሳሰድ መመዘኛን እንዲያከብሩ እና የዕርዳታ ድጋፍን ከማስተጓጎል እንዲቆጠቡ ይህንን ጥሰው ከተገኙ ደግሞ ሃይልን ያለአግባብ በመጠቀም እና ሌሎች ሰብአዊ ጥሰቶች የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸው ተመጣጣኝ እርምጃመስጠት ይጠበቅባቸዋል።

የሃገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስቴር የስደተኞች የከለላ ጥያቄን የሚያደናቅፉ ነገሮችን ይ ማስወገድ አለበት። ይሄም የጥገኝነት መጠየቂያ ቢሮን በካሌይ በመክፈት ወይንም በነባር ቢሮዎች ጥገኝነት ለመጠየቅ የሚፈልጉ ስደተኞች የሚስተናገዱበትን መንገድ ማመቻቸት ያካትታል። በካሌይ ያለመጠለያ ለሚኖሩት ከለላ ፈላጊዎች በተቻለ ፍጥነት መኖሪያ ለመስጠትጨምሮ ሌሎች ማንነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ የሌላቸው ስደተኞችም መሰረታዊ አገልግሎቶችን የሚያገኙበትን መንገድ ለማመቻቸት የሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው ኤጀንሲዎች እና የሰብአዊ ተራድኦ ቡድኖች ጋር በጋራ መስራት አለበት።

በመጨረሻም የአከባቢዉ እና የሀገሪቱ ባለስልጣናት የቤተሰብ ጥበቃ ለሌላቸው ስደተኛ ህፃናት በርካቶችን ሊያስተናግድ የሚችል እና በቂ ይሰው ሃይል ያለው መጠለያን ጨምሮ በቂ የህጻናት ከለላ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት አለባቸው።

# የመፍትሄ አቅጣጫ

## ለፈረንሳይ መንግስት

- የከተማዋ አስተዳደር እና የሃገር ዉስጥ ጉዳይ ሚንስቴር ስደተኞች በተኙበት እና ምንም አደጋ ሊያደርሱ በማይችሉበት ሁኔታ ላየ እያሉ  የፈረንሳያአድማ በታኝ ፖሊሶች እና ሌሎች የጸጥታ ሀይሎች የሚያቃጥል ፔፐር ስፕሬይ እና ሌላ ከመጠን በላይ የሆነ የሀይል ዕርምጃ እንዳይጠቀሙ አስቸካይ እና ቀጥተኛ ትዛዝ መስጠት አለባቸው።
- የካሌይ ከተማ አስተዳደሪዎች በሰኔ ወር የተላለፈዉን የፍርድ ቤት ዉሳኔ በፍጥነት በመቀበል የመጠጥ ዉሃ፣ የመጸዳጃ እና የገላ መታጠብያ መገልገያዎችን በማሟላት እንዲሁም የከለላ ፈላጊዎች እና ሌሎች ስደተኞችን መብት ለመጠበቅ ሌሎች እርምጃዎችን መዉሰድ አለባቸው።
- የሃገር ዉስጥ ጉዳይ ሚንስቴር ጥገኝነት ለመጠየቅ ለሚፈልጉ ስደተኞች በካሌይ ቢሮ መክፈት ወይንም ወደ ነባር የጥገኝነት መጠየቅያ ቢሮዎች በማጓጓዝ ከለላ መጠየቅ እንዲችሉ ማድረግ አለበት።
- የፈረንሳይ መንግስት የአዉሮፓ ህብረት በተጣለበት ግዴታ መሰረት እራሳቸዉን መደገፍ የማይችሉ ጥገኝነት ጠያቂዎች ጥገኝነት የመጠየቅ አዝማሚያ ማሳየት ከምጀመራቸው ጊዜ ጀምሮ በአስቸኳይ ተቀብሎ በማስተናገድ የጥገኝነት ሂደታቸው እስኪታይ ከለላ ማድረግ አለበት። መንግስት በካሌይ ያለመጠለያ ለሚኖሩት ማስረጃ አልባ ስደተኞች በተቻለ ፍጥነት ጊዜያዊ መጠለያ ለመስጠት መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት እና ከሰብአዊ ተራድኦ ቡድኖች ጋር በጋራ መስራት አለበት። ጊዜያዊ መጠለያው የግድ በሰሜን ፈረንሳይ ብቻ መወሰን አይጠበቅበትም።
- የአከባቢ እና የሀገሪቱ ባለስልጣናት የቤተሰብ ጥበቃ የሌለቸው ማስረጃ አልባ ስደተኛ ህፃናትን በአስቸኳይ በመለየት በፈረንሳይ ጥገኝነት መጠየቅ መብት እንዳላቸው እንዲነገራቸው እና አስፈላጊ ከለላ እንዲሁም በቂ የሰው ሃይል ያለበት መጠለያ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።
- የአውሮፓ ህብረት መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች ኤጀንሲ እንዳመላከተው መሰረት ያለው እና የተሻለ ተጠያቅነት እንዲሰፍን ፖሊሶች የመታወቅያ ፍተሻ በሚያደርጉ ግዜ የፍተሻ ቅጽ ማስሞላት አለባቸው። የፍተሻ ቅጹ ቢያንስ ፍተሻው የተደረገበትን ግለሰብ ስም እና ዕድሜ፣ የፍተሻው ህጋዊ ምክንያት፣ ዉጤቱ እና ፍተሻዉን የፈጸመው ፖሊስ ስም መያዝ ይኖርበታል።